# <u>እግዚአብሔር ፀረ- ኢትዮጵያኖችን በአጭር ይቀጫል</u>

ከቀመሩ ደሳለኝ

እግዚአብሔር የተመሰገነ፣ ስሙ ለዘለዓለም ከፍ ብሎ የሚጠራ አምላክ ክብሩ ይስፋ። ኢትዮጵያንና ሕዝቦችዋን ጎበኘ። የተበደሉና የተሰቃዩትን፣ የተጨነቁና የሚያለቅሱትን አማኞቹን አየ ።የኢትዮጵያንና ሕዝቧን ጨህት አዳመጠ፣ ፀሎታቸውን ሰማ፣ እነሆ "አንኳኩ ይከፍትላችኋል ጠይቁ ይሰጣችኋል" እንደተባለው ቸርነቱን፣ ርዳታውንና ፍትሐዊ መለኮቱ በኢትዮጵያ ላይ እየታየ ነው።

አምባገነኑን የወያኔ/ ሕውሓት የነፃ አውጭ ቁንጮ ተዋናኝ አቶ መለስ ዜናዊንና የክርስትና ሃይማኖትን ለፖለቲካ አገልግሎት ያዋሉትን ሽጉጥ ታጣቂ አባ ገብረመድህን እግዚአብሔር ከዚህ ዓለም በሞት እያከታተለ አስጠራልን ። የገደሉ ይገደላሉ፣ ያስለቀሱም ያለቅሳሉ ፍርዱ የእግዚአብሔር ነው ።እያሳየን ነው፡ እግዚአብሔር ይመስገን።

ኢትዮጵያን ለማሳነስ፣ ለመበተን፣ ሕዝቧን በቋንቋ ከፋፍሎና ለያይቶ፣ አባሮና አሰድዶ፣አስሮና ገድሎ ለመጨረስ የተነሳውን አረመኔ፣ ጨካኝና ሴረኛ ባንዳ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለውና ስብዕና የጎደለው አምባገነንን እግዚአብሔር አነሳልን። ለኢትዮጵያ የማይበጁትን አስወገደልን። ለተበደሉና ለጸለዩ የእምነት ሰዎች ጨህትና ፀሎት በአምላክ ተደመጠ። እግዚአብሔር ምስጉን ነው።

ኢትዮጵያ በአለፉት 21 ዓመታት እንደ አገር አልተመራችም፣ ሕዝብም እንደ ዜግነቱ አልተጠበቀም። የአገር ሉዓላዊነት ተደፍራል፣የአገር ታሪክ ተንቋል፣የብዙ ሺህ አምት ታሪክ የመቶ ተብሎ ትቀልብሷል፣ስላምና ደህንነት ታጥቷል፣ ሕዝብ በአገሩ ነፃነትና መብት ተነፍጎታል፣ በጭካኔ ተደብድቧል፣ታስሯል፣ተገሏል እንድሰደድ ተደርጓል።አያሌ ስቃይና መከራን እያየ፤ በረሃብ በበሽታና በመሰደድ የአገር ክብርና ኩራቱን አጥቶ እየተሰቃየና እያለቀ ይገኛል።

የኢትዮጵያ አገራዊ ክብር ተደፍሮ፤ ሃብት ንብረቷ እየተዘረፈ፣ እንደ አገር ያካበተቻቸውና የተዋዋለቻቸው ውሎች እየፈረሱ፣ ዳር-ድንበሯ እየተቆረሰ ፣አገረ ለሁለት ያለሕዝብ ፈቃድ ተከፍላ ፣ ብሔራዊ ክብር ተደፍሮ፣ ሕዝቧ ተዋርዶ፣ሰንደቅ ዓላማዋ ተራክሶ፣ ለም መሬቷ እየተሸነሸነና እየተሸጠ፣ ፀረ-ኢትዮጵያ በሆነ የማፊያ ቡድንና የውጭ ጠላቶች ቅጥረኛ እየተገዛችና እያስተዳደራት ትገኛለች። ይህን እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ላይ እንዲሆን አይፈቅድም። ጥበቃውን እያሳየ ነው።

በአለፉት ሃያ አንድ አመታት ኢትዮጵያ እንደ አገር አልተመራችም። አቶ መለስ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ የሆነ መሪ አልነበረም።በዚህ ወቅት መሪ የላትም። አቶ መለስ ዜናዊ በውጭ ኃይል እየተረዳና እየታገዘ ፀረ- ኢትዮጵያና ሕዝቧ የቆመ ፣ ኢትዮጵያን ያዳከመና የጎዳ ፣የማፊያ ወራሪ ቡድን አስተዳደርና ሥርዓት ነው። አቶ መለስ ዜናዊ የዚህ ኢጋሚድ መሪ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላትና አጥፊ በመሆን ኢትዮጵያና ህዝቧን እጅግ ያሰቃየና የበደለ የግፍ ስራዎችን የፈጸመና ያለፈ ፋሽስትና ፋሽስታዊ ሥርዓት ነው።

በዚህ ፋሽስታዊ ተግባር፣ በደረሰበት ግፍና በደል ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር አዘውትሮ ጮሃል፣ ፀልዮል።የተለያዩ የእምነት ተከታዮች፤የክርስትናው በየቤተክርቲያኑና ገዳማቱ፣ የእስልምናው በየመስጊዱ ሁሉ ለፈጣሪ አምላኩ በጾም በፀሎት ቀን ከሌሊት ተማጽኗል፣ አመልክተዋል፣ አልቅሷል፣ርዳትና ጥበቃውን ጠይቋል። በዚህም የአምላክ ፈቃዱ ሆኖ አምባገነኑን ከነፖለቲካ አጋዡ የክርስትና ሃይማኖት መሪ ተብየውን በሞት ጠርቷል።

የእነዚ ሁለት ሕገ ወጥ ግለሰቦች እየተከታተሉ ከዚህ ዓለም መሞትና መለየት የእግዚአብሔር ልዩ ተአምርና የእሱ የበላይ ምስጥራዊ ጥሪ ነው። ይህን ተአምር በውል እንድንረዳውና እንድንገነዘበው፣ በጨቋኙም በተጨቋኙም ልብ ሊባልና ትምህርት ሊገኝበት፣ ልንጸልይና ለሥራችን ሁሉ ንሰሃ ልንገባ፣ እንደሰው ልናስብና የፈጣሪ አምላክን ሕግጋቶች ልናከብር ይገባናል።የአምላክ ቁጣ ይቀጥላል፣ ፀረ-ኢትዮጵያ ሁሉ ይገረሰሳሉ።

አምባገነን ሁልጊዜ ሁሉ ነገር በእሱ ቁጥጥርና በእሱ ኃይል ሁሉን ያሸነፈ ዘለዓለማዊ ይመስለዋል። አቶ መለስ ዜናዊ እግዚአብሔርን የሚያውቅ አይመስለኝም፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር የለውም። ፀረ-ኅብረተሰብ የሆነ ጨካኝነቱን አስተውለናል። የአገር ታሪክ ቀልባሽ፣ የህብረተስብ ከፋፋይ፣የብዙ ሰዎችን ሕይወት የአስጠፍ ነው። ተከታዮቹም ጥቅምና ስልጣንን

በግብዝነት ተቀብሎ ለአምባገነን መሪው በማጨብጨብና በአጉል ድንፋታ ታግለን ያገኘነው ብሎ በቀቢጠ ምኞትና ማን አለብኝነት በጭካኔ አገር እያጠፋና እየገደሉ መኖርን የሚመኙ ግብዞች ስለሆዳቸው እንጂ ሰለ ሕዝብና አገር የማያቁና የማይረዱ ባንዳዎች ናቸው።

የእግዚአብሔር ምስጢርና ተዓምራቱ ይቀጥላል። ልብ ያለ ልብ ይበለው። እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን እየጎበኘና እየባረከ ነው። እምነቱን ላጡትና ለማይከተሉት ቁጣው ሲመጣ ማልቀስና ማዘን ይሆናል። ተቀጣሁ ከማለት ፈሪሃ እግዚአብሔርን በልብ አሳድሮ መልካሙን መስራት፣ ጎዳና ተዳዳሪዎች፣ቦዘኔዎች፣ድሆች ብሎ ሰውን፣ ዜግነትና ሙብት ማሳጣት ነውር እንደሆነ ማወቅና መረዳት ከእግዚአብሔር ቅጣት ያድናል። ወ/ሮ አዜብ በአምባገነን ባለቤቷ ሞት ተቀጣሁ እያለች የአምላክ ቁጣ እየገለጸች ፣ ቤቱ ቀዘቀዘ፣ የባንዳዎች ሥርዓት አልጋው ፈረሰ ማለቷ መሰለኝ የሃዘን ሙሿቸውን ደረት በመንካት እምባ የሌለው ጩሀት በማሰማት ዋሃታው ተመልክቷል።

በአቶ መለስ ዜናዊ ሞት ብዙ ለማየትና ለመስማት ለመታዘብም ተችሏል። ከአልሞተም፣ ሞተ የተከታተሉ ውሸትና፣ የተለመደ ክህደት ሲሆኑ በአቶ መለስ አስክሬን ላይ ጨርቅ እየተባለ የተፌዘበት፣ ያዋረደውና ያራከሰው፣ሊቀይረው የተመኘውን አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ሙት አካሉ እንድለብሰው መደረጉና ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጋር ትይዩ የሕውሓት/ የትግራይ የክልል መለዮ በአስክሬኑ አካባቢ በዘቦቹ ተይዞ መታየቱ ነው።

በሌላ በኩል ተቃዋሚ ነን የአቶ መለስን አስተዳደርና ሥሪዓት እንቃወማልን ፣ ይህን የቋንቋ ጎጠኛ የገገር ታገለን እናሸንፋለን የሚሉት በአብዛኛው ማዘናቸውና በሰውየው ሞት የተቆጩ መሆናቸውን በግልጽና በገሃድ ሲናገሩ ተሰምቷል። ዶ/ር ብርሃኑ እጅግ የተደናገጠ ሆኖ ሲታይ ወ/ሮ ብርቱካን ተክዛለች፣ግራ የተጋባች ሆና ሃዘኗን ስትገልጽ አቶ እሰዬ ደግም በጣም የተቆጨና የአቶ መለስ ሞት እጅግ እንዳሳሰበው በቃለ መጠይቅ ላይ ብዙ ያለበት ነው። የጀመረውን የግድብ ሥራና የልማት እቅዶቹን ቢጨርስ ጥሩ ነበረ በማለት የጓደኛውን ሞት ሃዘን በተሞላበት ስሜት በመናገር ንግግሩን ደምድሟል። ይህም ልማት ሳይሆን ኢትዮጵያን ከፋፍሎና ሸጦ ማለቱ እንደሆነ ከወያኔ ሕሌናው ለመረዳት ይቻላል።

ከአቶ እሰዬ አብረሃ እንኳን ከዚህ የተለየ አይጠበቅም። በጥቅም ተቀያይመው ተለያዩ እንጂ ወያኔነቱና በፀረ-ኢትዮጵያና ሕዝቧ ላይ አንድ አይነት አቋምና ባህሪ አላቸው፤ኢትዮጵያን የተዋጋና ኤርትራን ያስገነጠለ፣የባህር በሮቿን ያሳጣ፣ጦርነትን መዋጋትና መፍጠርም እንችላለን እያለ የሚፎክርና የወያኔ/ትግራይ ነፃ አውጪ ታጋይ እንደሆነና አሁንም በዚያው ልቡ እንደሆነ እናውቃለን። የሚያሳዝነው ግን አቶ እሰዬን ተቃዋሚ ነው ብሎ የሚከተለው ተላላና ውዥምብር ተቃዋሚ ተብዬዎች የሱ ተከታይና አጨብጫቢ መሆን ነው።

አቶ እሰዬ አብረሃንና ሌሎች በተቃዋሚ ዙሪያ ነን ፣ የአቶ መለስን ሥርዓት እንቃወማለን በማለት ተቃዋሚውን የሚያታልሉ እንጂ፣ የምር የዚህ የወያኔ ተቃዋሚዎች እንዳልሆኑ በዚህ ወቅት መረዳትና አቋምህን ማስተካከል ይኖርብሃል። ወያኔ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ጠላት ነው ። ለዚህ አጥፊ ድርጅት ጉጉትንና ጸጸት ያለው ድርጅትም ሆነ ግለሰብ ለኢትዮጵያ አይበጅም፡ እግዚአብሔርም የሚቆጣበትና የሚቀጣው ነው።

የወያኔ/ኢሃድግ ሥርዓት ፀረ -ኢትዮጵያ፣ፀረ-ህብረተሰብ ፍሽስታዊ ነው። አቶ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን ያዋረደ፣ አገር የሸጠ ባንዳ እንጂ የልማትና የእድገተ ሰው አልነበረም። የብዙ ሰዎችን ሕይወት ያስጠፍ ነብስ ገዳይ ውንጀለኛ ሰው ነበር። ፍሽስታዊ ሥራት የመራ ባንዳ ነበር ።በዚህም ወንጀል ሙት አካሉ ይጠየቅበታል፣ይወቀሳል።በመጥፎ ታሪክ የተመዘገበ ሥራ ያለው ሰው እንጂ አቶ መለስ የልማት አይደለም። አቶ እሰዬ የተመለከተበት ዓይን በባንድ ህሌናው ይመስለኛል፤ መንገድ፣ ድልድይ ወይንም ህንጻ መስራት በፍሽስት ጣሊያን የአምስት አመት ውረራ የታየ ነው። ይህ የባንዳዎችና የግብዞች መገዛትን ለሚያፈቅሩ የነበረና ያለ ነው።የወያኔ ታርክ የመጥፎ ታርክ ጥቁር ነጥብ ነው። አቶ መለስ በዚህ መጥፎ ታሪኩና በጠላትነቱ ይታያል።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የገላገለውን አምብገነን በደስታና በእልልታ የሚያከብርበት ውቅት ነው። ነገር ግን ሕዝብ እየተገደደ በየመንደሩ ድንኳን ጥሎ እንዲያለቅስ በግድና በሃይል እዲያዝን እየተገፋ እንደሆነ ይስተዋላል። ይህ የወያኔዎቹ ለቅሶ እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም።የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጭ ለብሶ በደስታ የሚታይበት፣ ወያኔዎች ጥቁር ለብሰው ለቅሶና ሃዘንን የሚቀበሉበትና የሚያዩበት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንካራና ብርቱ መሆን ይጠበቅብሃል፡ አድርባይ ሆነህ  በውሸት ማልቀስ ደረትህን መምታት የለብህም። የውሸት ሙሾና ማርገድ ባህልህና ልምድህ አይደለም። ከሁሉም በላይ እግዚአብሔርን እንዳታስቀይም ተጠንቀቅ፡ ይህ አሁን እየተፈጸመ ያለው የአምላክ ተዓምር ነው ። ለኢትዮጵያና ለንጽሕ ሕዝቧ በግፍ ለፈሰሰው ደምና ያለአግባብ ለአለፈው ሕይወት የእግዚአብሔር ፍርድ፣ጥበቃና የመዳን ተስፍ ጅማሮ ነው። ጾምና ጸሎትህን በፅናት ቀጥል እግዚአብሔር ለሃይማኖቱም ለኢትዮጵያ መልካሙን መሪ ይሰጣል ። ኢትዮጵያን ይጠብቃል ጠላቶቿንም ቀድም ይገስጻል።

## እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ምንጊዜም ይጠብቃል!

ነሐሴ 19/2004